EthioLion

# የፍቅር ክፍያ (በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ አጭር ትውስታ)

ከአህመድ ይማም

ሀምሌ 6 ቀን 1983። አዲስ አበባን የጭንቅ ጽላሎት አጥሎባታል።

ይህን አዲስ አበባን ጨምሮ መላው ሀገሪቱን ያለበሰ የፍርሃት ዳመና ተዳፍረው ያን ዕለት ወደመሥሪያ ቤታቸው ለመሄድ መንገድ ከጀመሩት አንዱ ነበርኩ። ከባልቻ ሆስፒታል ተነስቼ፣ ፖሊስ መምሪያ አለፍኩና ወደ ለገሃር አቀናሁ። ከሌሎች መንገደኞች ጋር መብራት ኃይል ጎን ካለው ኬክ ቤት አጠገብ፣ ሊስትሮዎች ወንበራቸውን ደርድረው ጫማ ከሚጠርጉበት ቦታ ደረስን። ካንድ አምስት አይበልጡም ለስራ በጠዋት መቀመጫ ወንበሮቻቸውንና የሊስትሮች ሳጥኖቻቸውን የደረደሩት ልጆች። የቁጥራቸውን ማነስ ሳይ "ከየት አምጥተው ጉሮሯቸውን ይዘጉ ይሆን?" አልኩና ለራሴ ጥያቄ አቀረብኩ። በሊስትሮነት የሚሰሩት ልጆች ረጂ የሌላቸው ወይም ከችግርተኛ ቤተሰብ የሚመጡ መሆናቸውን እያሰብኩ።

ይህንኑ እያሰላሰልኩ ከኬክ ቤቱ በስተግራ በኩል አልፎ ወደገነት ሆቴል የምትሄደውን ጠባብ መንገድ ልሻገር ስል አንድ ጥይት ወደ ሰማይ ተተኮሰ። የተተኮሰው ሜክሲኮ አደባባይ አጠገብ ቆሞ ፊቱን ወደ ትምባሆ ፋብሪካ ያዞረውን ታንክ ከሚጠብቁት ሁለት የወያኔ ወታደሮች በአንዱ ነበር። መንገዱን ልንሻገር የነበርነው ወደ 15 የምንሆን ሰዎች ቀጥ ብለን ቆመንና ወደ ኋላችን አፈገፈግን። ስለተኩሱ ይበልጥ ለማጣራት ወደ ታንኩ ዓይኖቼን ወረወርኳቸው።

የደም ግብሩን እንደ ለመደው ሊጠጣ ወያኔያዊው ጭራቅ የመሣሪያውን ላንቃ ከፍቶ ነበር። ታንኩ ከቆመበት አደባባይ ማዶ፣ በስተቀኝ በኩል ካለው፣ ሸንበቆ እጅብ ብሎ ከበቀለበት አጥር አጠገብ ሁለት ሰዎች አሉ። አንዱ እጁን ወደላይ አድርጎ ወደታንኩ ይራመዳል። መሳሪያውን በሁለቱ ሰዎች ላይ ደግኖ፣ ወደኋላው የሚያፈገፍገው አንዱ የወያኔ ወታደር "እጅህን ወደላይ አድርገህ ና!" የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶት ይመስላል። ሌላው ሰውዬ ደግሞ የሚያደርገውን አጥቶ፣ በግቢ ነፍስ፣ በውጭ ነፍስ፣ በደመ-ነፍስ ይርበተበታል።

ብዙም አልቆየ። የተደገነው የወያኔው መሣሪያ እጁን ወደላይ ባደረገው ወገን ላይ በሩምታ ተተኮሰ። ነፋስ ወደላይ አንስቶት፣ ልክ ቀስ እያለ ከመሬት እንደሚያርፍ ሸማ ያ ከሰከንድ በፊት ህያው የነበረ ሰው ተንገዳገደና ሽብልል ብሎ ከመሬት ወደቀ። ሌላውም ሰውዬ ላይ ተተኮሰ። ከአጥሩ ስር ኩርምት ብሎ ወደቀ። ከሁለቱም ደም ኩልል እያለ በአስፋልቱ ላይ መፍሰስ ጀመረ። አዲስ አበባ ገና በጠዋቱ ሁለት ልጆቿን ገበረች።

ወደ ኋላ ተመለስኩ። በተግባር ዕድ በኩል አድርጌ፣ አደባባዩን በስተቀኝ በመተው ወደ ለገሃር መንገዴን የቀጠልኩት አፌን ደም ደም እያለው ነበር። ጠላይ ታስሮ የነበረው መቶ አለቃው ወንድሜ በቀደምለታ ልጠይቄው ሄጄ አየሁት ያለኝ ህልም ትዝ አለኝ። እናታችንን ለመጠየቅ ክፍለ-ሀገር የሄደ ይመስለዋል።

"ወደ ወላጆቻችን ግቢ ስገባ ድንኳኖች ተጥለዋል። ግቢው ግን ጸጥ ረጭ ብሏል። እናታችንን ሳያገኛት ..." በማለት ስላየው ህልም ይነግረኝ ጀመር። ቀጠለ "'እንኳን መጣህ። ልጄን ልድር እኮ ነው! እንኳን መጣህ' አለችኝ እንዳየችኝ" በማለት።

"ማን ነው የሚዳረው?" ብዬ ጠየቅኋት።

"ምን ቸገረኽ! እንኳን መጣህ! ትንሹ ወንድምህን ልድር ነው።" ብላ ስትመልስለት ነበር ብንን ያለው። በላብ ተጠምቆ። ህልሙን ሲነግረኝ አደጋ እንዳይደርስብኝ ያለውን ፍርሃት ገልፆ ጥንቃቄ እንዳደርግ ከምክር ጋር ነው። ስንለያይም

እስከመጨረሻው እንደሚለያይ ሰው አንገቴ ላይ ተጠምጥሞብኝ፣ አገላብጦ ስሞኝ ነበር። አሳዘነኝ። እንደ ማንም ወንጀለኛ ለሀገሩ በፖሊስነት ከ30 ዐመታት በላይ ባገለገለ መታሰሩ አንሶ ለእኛ መጨነቁ አስጨነቀኝ። ይህንኑ እያሰብኩ፣ ከወላጆቻችን በተጨማሪ፣ የእሱንም ቤተሰቦች የመርዳት ሃላፊነት በእኔ ላይ መውደቁን እያሰላሰልኩ ነበር ሳላውቀው ቢሮ የደረስኩት።

ግማሽ የሚሆኑት የሥራ ባልደረቦቼ ዛሬ አልገቡም። ለነገሩ እኔም በሰበቡ የከተማውን ሁኔታ ወጣ ብዬ ለማየትም ነበር ወደ ሥራ የሄድኩት። እንኳን ከተማዋን ጭንቅ ውጧት አምቦ በወያኔ ከተያዘች ወዲህ ለወትሮውም የቢሮ ሰዓታችንን ባብዛኛው የምናሳልፈው በወሬ ነው። ያን ቀንም የገባነው ጥቂት ሰራተኞች የዋልነው በየአካባቢያችን የተፈፀሙ አዳዲስ ክስተቶችን እየተቀባበልን ስናወራ ነበር።

"እኛ ሰፈር አንድ ወጣት በቀይ ሽብር ጊዜ ህጻን እያለ አባቱን የኢሕአፓ አባል ነህ ብሎ የገደለበትን የደርግ ካድሬ ገድሎ ደሙን ተወጣ። ...እኛ አካባቢ ደግሞ ወያኔዎች አንድ ሰውዬ በሌሊት ከቤቱ አውጥተው ገድለውት ሌባ ገደለው አሉ። ..." ሁላችንም የምናውቀውን እየተቀባበልን ስንነጋገር ዋልን። የግድያ፣ የጭንቀት ወሬ። በመንግሥቱ ወንበር የተተኩት አዲስ ገዢዎቻችን ጋር ንክኪ እንዳላቸው የምንጠረጥራቸው ጥቂት ባልደረቦቻችን ወሬ ለማነፍነፍ ሲመጡ እየተጠነቀቅን። በተለይም ከበረከት ስምዖን እና ከታምራት ላይኔ ጋር ወዳጅነት አለን እያሉ ካሁኑ ታማኝነታቸውን እያሳዩ ያሉት ሁለት ሰዎች - ታዬ እና ሙሉጌታ ሲመጡ የምንነጋገረው እየተጠነቀቅን ነበር። ሁለቱም መስሪያ ቤቱ ውስጥ የነበረው የኢሠፓ መሰረታዊ ድርጅት ምልምል አባል ሆነው ሙሉ ተቀባይነት ለማግኘት ሲያደፈድፉ እንደነበር የሚያውቀው ሰራተኛ በግርምት እየታዘበ ፊት ነስቷቸዋል። አዲሱ ከበሮ የሚደለቅለት የዘመኑ የጎሳ ፖለቲካም ከመቅጽበት የለከፋቸውም ጥቂት ሰራተኞች ነበሩ። በምሳ ሰዓት ሰብሰብ ብለን ስንጨዋወት፡

"እንደ ኢትዮጵያ ባለች ባለብዙ ቋንቋ ሀገር ዘርን ከሀገራዊነት አስቀድመን የት ልንደርስ ነው?" አልኩኝ ውይይታችንን ወደ አጠቃላይ ርዕስ ለመውሰድ።

"እኛ ኦሮሞዎች ተጨቁነናል! መብታችን መከበር አለበት!" ጀማል ረገጥ አድርጎ ተናገረ። "አጀኢብ!" አልኩኝ ለራሴው። የሰው እንዳ ፈጥኖ በየወቅቱ የሚመጡት ገዢዎች የሚያቀርቡለትን የፖለቲካ ጥብቆ ለመልበስ መሽቀዳደም አስገርሞኝ።

"ጭቆናን ለማጥፋት የግድ ኢትዮጵያዊነትን አውልቀን መጣል የለብንም እኮ። አሁን አንተ ግማሽ ኦሮሞ፣ ግማሽ አደሬ ነህ። ማን ተብለህ፣ እናትና አባትህን ልታገናኛቸው ነው? ዘርን ብቻ ግንጥል ጌጥ ማድረጉ ችግር ያለው ይመስለኛል።" በጥያቄ መለሰችለት መሰረት። ሌላው ባልደረባችን ሌላ ጥያቄ አቀረበለት ለጀማል፡

"እንደውም በአንዱ አያቴ ከጎጃም የቄስ ዘር ነኝ ስትል አልነበረም እንዴ?" በማለት።

"መምረጥ ዴሞክራሲያዊ መብቴ ነው፣ ኦሮሞነትን ወይም አደሬነትን" መለሰላት።

"የግድ እኮ እናትህን ለመውደድ አባትህን፣ ወይም አባትህን ለመውደድ እናትህን መጥላት ያለብህ አይመስለኝም" አለችው በንግግሯ ይመስለኛል ማለት የምታዘወትረው መሰረት። በመካከሉ ታዬ በአጭር ቁመቱ እየተድበለበለ መጥቶ፣ ሹክክ ብሎ ሲገባ የውይይታችንን ርዕስ ባንቀይረው ኖሮ ክርክሩ ወደየት እንደሚያመራ አላውቅም። ዝምታችን ሲበዛበት እንደሌሎቹ መስሪያ ቤቶች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቋቁመን በአለቆቻችን የደረሰብንን በደል መፍረድ እንዳለብን ሊመክረን ሞከረ። በተራቢነቱ የሚታወቀው የሽጥላ፡

EthioLion

“ታዬ ቅሬታም ካለ አንተ የኢሠፓ ምልምል አባል በመሆንህ ብቻ ሳትወዳደር የቡድን መሪ መሆንህ ነው” ብሎ ሲቀልድበት ሁላችንም ሳቅና ወደሌላ ጭውውት ሄድን። እንዲህ እንዲህ እያልን ከሥራ መውጫ ሰዓት ደረሰ።

ከቀኑ በ11 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ላይ ከመስሪያ ቤቴ ወጥቼ ከሁለት ጓደኞቼ ጋር ተከራይተን ወደምንኖርበት ቤት በታክሲ አመራሁ። ሜክሲኮ አደባባይ ጋር ስንደርስ ፊቴን ጠዋት የተገደሉት ሰዎች ወደወደቁበት በኩል አዙሬ ተመለከትሁ። ጠዋት ያልነበረ ከጎናቸው አንዳንድ ቦንብ ተቀምጦ አስከሬናቸው ተዘርግቷል። ቦንብ ሊጥሉ ሲሉ ተገደሉ ለማለት መሆኑ ነው። ጠዋት ሳልፍ ያልነበረ የአንድ ታዳጊ ወጣት ሬሳ ደግሞ ፖሊስ መምሪያ ፊት ለፊት ወድቋል።

“ይህ ደግሞ በአካባቢው ሰልፍ ያደርጉ በነበሩ ወጣቶች ጋር ቦንብ ይዞ ተገኝቶ የተገደለ ነው። መርካቶ፣ አብነት፣ ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት፣ ፒያሳ፣ በቅሎ ቤት አካባቢ ወያኔ ኤርትራን በተመለከተ የሚያራምደውን ሰላማዊ ሥራ በመቃወም ሰልፍ የወጡ ፀረ-ሰላም ወጣቶች ተገድለዋል።” አለና አንዱ ተሳፋሪ ተናገረ - በምጓዝባት ታክሲ ውስጥ የነበረውን ዝምታ ሰብሮ። የሁላችንም መልስ ዝምታ ሲሆንበት “ወያኔ ሌባውን ሁሉ አጠፋው። እጅ ከፍንጅ ሲያዙ ወዲያው እርምጃ እየወሰደ…” በማለት ቀጠለ ያው ፀጉሩ ጎፈር ያለ ሰው።

“ይህ መመሪያው አጠገብ ቦንብ ይዞ ተገደለ የተባለው ህፃን እዚያች ኬክ ቤቷ አጠገብ ጫማዬን ይቀባልኝ የነበረ የረዢም ጊዜ ደንበኛዬ ነበር” በማለት መለሱለት - ካጠገቤ የተቀመጡት አዛውንት በሃዘን ጭንቅላታቸው እየነቀነቁ።

“ቢሆንስ ሌባ ተይዞ ወደ ፍርድ ቤት ይወሰዳል እንጂ መገደሉ ተገቢ ነው?” ሌላዋ እናት ተሳፋሪ በትዝብት ጠየቁት።

“ወዲያው እርምጃ ካልተወሰደባቸው እኮ ከተማዋን በዝርፊያ ሊያውኳት ነው! ይበላቸው!” ብሎ ባለጎፈሬው ጎን ያለው ሌላው ወጣት መለሰላቸው።

“ከመስረቅ ይልቅ መግደል ከተማዋን ይበልጥ አያውካትም ብለኽ ነው የእኔ ልጅ?” ረጋ ብለው ጠየቁት - እኔ አጠገብ ያሉት አዛውንት። ያው ወጣት መናገር ሲጀምር ነበር ከመውረጃዬ ደርሼ ከታክሲዋ የወረድኩት።

የክረምት ዕረፍቷን እኔ ጋር ልታሳልፍ ከክፍለ-ሀገር የመጣችው የወንድሜ ልጅ፣ አስናቀች “ጋሼ፣ እባክህ በጊዜ ወደቤት ና” ማለቷን አሰብኩና እንዳታስብ በቀጥታ ወደቤቴ ገባሁ። ጭንቀቷን ሳስብ ወንድሜ (አባቷ) ስላየው ህልም ለእሷ መንገሬ ጥፋት እንደ ሆነ እያሰላሰልኩ ነበር በፈጣን እርምጃ እቤት የደረስኩት።

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቭዥን እንደሆነ እንደ ደርግ ጊዜው የአዲሶቹን ገዢዎች ቀረርቶ ነበር የሚያቅራሩት። ያው የምናየውን የሀገራችንን የጨለመ የሕይወት ትዕይንት በዜና መልክ የምንሰማው ከውጭ ሬዲዮ ጣቢያዎች ነበር። ያን ቀን ጀርመን ሬዲዮ ጣቢያን ለመስማት የመተላለፊያ ሰዓቱ አልፎ ነበር እቤት የገባሁት። ምንም እንኳ በወቅቱ የሀገራችን ሕይወት ላይ ቁርጡ ያለየለት ጥቁር ደመና ቢያጥልበትም አስናቀች የጭውውታችን ጨው ሆና ምሽቱን ገፋነው። ከቤተሰባችን እንደ እሷ ጨዋታ የሚያውቅ የለም። በውብ መልኳ ላይ፣ የወተት አረፋ መስለው በልክ ከተደረደሩት ጥርሶቿ እና ጥርት ብለው ከሚያበሩት ትላልቅ ዓይኖቿ ጋር የቅንነት ፈገግታዋን እየረጨች፣ በምትፈጥራቸው ቀልዶች ሕይወትን ታበራለች። ብሉልኝ፣ ጠጡልኝ ስትል ደግነቷ የተራበን ያጠግባል።

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሊሆን 5 ደቂቃ ያህል ሲቀረው ወደሽንት ቤት ሄድኩ። ጣጣዬን ጨርሼ የዕለቱን ሁኔታዎች ዘገባ ከአሜሪካ ጣቢያ ላይ ለማዳመጥ። ከጓደኞቼ ጋር

EthioLion.com

EthioLion

በግል ተከራይተን የምንኖርበት ግቢ ተከራዮች በሙሉ የምንጠቀምበት አንድ የጋራ ሽንት ቤት አለ። ከቤት ልወጣ ስል አስናቀች፣

“ጋሽዬ ቡናው ደርሷል። የት ልትሄድ ነው?” አለችኝ - ስኒዎቹን እረከቦቱ ላይ እየደረደረች እና በስስት እያየችኝ።

“መጣሁ፤ ሽንት ቤት ደርሼ” አልኩና ቢጃማዬን እንደለበስኩ ባትሪዬን ይዤ ስሄድ ሽንት ቤቱን ሌላ ሰው ገብቶ እየተጠቀመበት ነበር። ባትሪዬን ከማብራቴ “ሰው አለ” ብለው መለሱኝ - የግቢያችን አድባር እማማ አበበች።

ሰዓት ደርሶ የአሜሪካ ሬዲዮ እንዳያመልጠኝ ቸኮልኩ። ወደውጪ ወጣሁና ከግቢው አጥር ጥግ ሽንቴን መሽናት ጀመርኩ። በመካከሉ ከጎን በኩል ካለችው ቀጭን የሰፈሩ መንገድ ሁለት ሰዎች ወጥተው እኔ ወዳለሁበት መጡ። ያን ሰሞን ከምሽቱ 1 ሰዓት ጀምሮ ሰዓት ዕላፊ ተጥሎ ነበር። ከእኔ ጋር የሚኖሩት ሁለቱ ጓደኞቼ መጠጥ ቤት አዘግተው እየጠጡ ያመሻሉ። ብመክር ብመክር አልሰማኝ ብለዋል። እንዳይያዙ ወደቤት በዚያ በኩል እየተሽለኮለኩ እንደሚመጡ አውቃለሁ። ሁለቱ ሰዎች እነሱ መሰሉኝ። ከሁለት ቀን በፊት አንደኛው በስካር “እነኝህ ሌቦች! ገዳዮች! ምትክ ፋሽስቶች! ... “ እያለ ሲሳደብ ተቆጥቼ ወደቤት እንዳስገባሁት ትዝ አለኝና ምክሬን አልሰማ ብለው እራሳቸውን ለአደጋ ማጋለጣቸው አናደደኝ። ፊቴን ወደ እነሱ አዙሬ ባትሪዬን ሳበራ፣

“ማን ነህ? ባለኸበት ቁም!” ብሎ አንባረቀብኝ - ከሰፈሯ መንገድ ከወጡት አንደኛው።

“እጅ ወደላይ! ፊትህን አዙረህ ወደቀበሌ ሂድ!” ብሎ ድጋሚ ጮኸብኝና ሮጠው፣ አጠገባቸው ካለው የኤሌክትሪክ እንጨት ስር ተከለሉ።

“እኔ ነኝ፣ ባየህ” ብዬም ንግግሬን ሳልጨርስ ነበር አንድ ጥይት የተተኮሰው። ፊቴን ወደምኖርበት ቀበሌ 03 ወደሚወስደው አስፋልት መንገድ ሳዞር አንዱ፡

“እንዳትተኩስ ባትሪ ነው የያዘው!” ሲል ከጆሮዬ ገባ። “ተበላሁ!” አልኩኝና እጄን ወደላይ አድርጌ ወደተባልኩት አቅጣጫ መንገድ ጀመርኩ። ብዙም እርምጃ ሳልሄድ ነበር እቤት ጥያቄው የወጣሁት ቤተሰቦቼ እየተንጫጩ ግር ብለው ሲወጡ የተደመጡኝ። አስናቀች፣ ሰራተኛዬ፣ ሬዲዮ ለመስማት እኔ ቤት የተሰባሰቡት ጎረቤቶቼ እኔን ወደቀበሌ ሂድ ካሉኝ ሁለት ታጣቂዎች ኋላ እንዳሉ አሰብኩ።

“ጋሽዬ! አንትዬ! እኔን! እኔን! ... “ የወንድሜ ልጅ አስናቀች ኡኡታውን አቀለጠችው።

“ቀጥ ብለህ ሳትንቀሳቀስ እጅህን ወደላይ አድርገኸ ወደቀበሌ ሂድ!” ብሎ ከተኮሱብኝ አንዱ ዳግመኛ ሲያዘኝ ሁለቱ የወያኔ ታጣቂዎች ከኋላዬ እንደተከተሉኝ ታወቀኝ። ጥቂት ሜትሮች ርቆ ካለው አስፋልት ማዶ “ማን ነው! ምንድነው! ... ብለው እየተንጫጩ የሌላው ቀበሌ ታጣቂዎች እኛ ወደ አለንበት ሲመጡ ተሰሙኝ።

ከእኔ አልፎ በቤተሰቦቼ ላይ አደጋ እንዳይደርስ አሳሰበኝ። በአንድ ነገር ላይ ሃሳቤን ለማቆየት ብዙም ጊዜው አልነበረኝም። ሳላስበው የተፈጠረው አስቸጋሪ ክስተት ሁኔታዎች ከመቅጽበት የሚለዋወጡበት ሆነብኝ።

“ቁም እንዳትንቀሳቀስ!” የሚል ሌላ ትዕዛዝ ከአስፋልቱ ማዶ ካሉት ታጣቂዎች አንባረቀብኝ። ከዚያው በኩል “እጅ ወደላይ! ቁም!” ሌላው ጮኸብኝ።

"ጋሽዬ አጥር ጥግ ያዝ! ጋሽዬ አጥር ጥግ ያዝ! …" ነፍሷ እስከምትወጣ የምትወደኝ አስናቀች ትጮሃለች ከኋላዬ። ፖሊሱ ወንድሜ ጋር ሆኜ ትምህርቴን ሰከታተል አብራኝ ነው ያደገችው። ለእኔ ያላት ፍቅር ልዩ ነው። ከትልቅ እህቷ ጋር ሁልጊዜ ሲጣሉ አስታውሳለሁ - ትልቋ የእናቷን ወንድም እያሞካሸች፣ አስናቀች ደግሞ እኔን።

ከፊቴም ከኋላዬም "እንዳትንቀሳቀስ!" ተብዬና መሳሪያ ተደግኖብኝ ያጥር ጥግ ለመያዝ መንቀሳቀሱ ያለው አደጋ ታሰበኝ። ይልቅስ በቤተሰቦቼ ላይ ያለውን አደጋ ለመቀነስ ባለሁበት ቆሜ "ቤተሰቦቼ ናቸው!፡ ቤተሰቦቼ ናቸው! …" እያልኩ ተናገርኩ - ሰሚ ባገኝም ባላገኝም። እንደበራ ያለውን ባትሪ ወደላይ ይገፍ፣ የደመ ነፍሴን "ቤተሰቦቼ ናቸው! ቤተሰቦቼ ናቸው! …" እያልኩ ደጋግሜ መጮኼን ቀጠልኩ።

ብዙም አልቆዩ። በእሩምታ አስፋልቱ ማዶ ካሉት በኩል ከፊት ለፊቴ ተተኮሰ። ታፋዬ ላይ ትኩስ ፈሳሽ ነገር አራሰኝ። እግሬ ሰውነቴን መሸከም አቅቶት አቅሜ እየደከመ መጣ።

"ወይኔ! ጋሽይዬ! እኔን! እኔን! …" እያለች የምትጮኸው አስናቀች ድምጽ ወደእኔ እየቀረበ ሲመጣ ጥርሴን ነክሼ ወደእሷ ዞርኩ። አንዲት እርምጃ እንደሄድኩ ነበር አቅም አንሶኝ ወደሁዋላ የወደቅሁት።

የአስናቀችም ድምጽ እየቀረበኝ እየቀረበኝ የመጣ መሰለኝ። ዓይኔን እሷ ወዳለችበት ለመወርወር ሞከርኩ። ሌላ ተኩስ ተከተለ። "እ!" ብላ አስናቀች የሲቃ ድምጽ አሰማችና እላዬ ላይ ወደቀች።

"ወይኔ እህቴን አስገደልኩሽ!" የመናገር አቅሜን አሰባስቤ ጠየቅሁዋት።

"ደ … ደ..ህ … ና …"ድምጿ እየተቆራረጠ መናገር ጀምራ ፀጥ አለች።

EthioLion
EthioLion.Com